# በኢትዮጵያ የአምስተኛ ዙር አገር አቀፍ ምርጫ ዝግጅትና የባለድርሻ አካላት ቀጣይ ሚና

· JAN 23RD, 2015 · 0 COMMENT

በኢትዮጵያ የአምስተኛ ዙር አገር አቀፍ ምርጫ ዝግጅትና የባለድርሻ አካላት ቀጣይ ሚና

(በፋና ብሮድካስትንግ ኮርፖሬሽን ተዘጋጅቶ በ 13/05/2007 በሼራተን አዲስ ሆቴል በተሄደው ሀገር አቀፍ ኮንፈረንስ በአቶ ጥላሁን እንደሻው የመድረክ የሕ/ግ ኃላፊ የቀረበ)

*መግቢያ*

በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ በርካታ መንግሥታት በምርጫ የመንግሥታቸውን ሕግ አውጪ አካላት በማቋቋም ሀገሮቻቸውን ማስተዳደር ከጀመሩ ብዙ ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡ ይህም ከጥንታዊ የግርክ ከተሞች ማለትም ከባሪያ ገዥዎች ዘመን ጀምሮ ማለት ነው፡፡ ከዚህም ሌላ የተለያዩ ማሕበረሰቦች ባቋቋሙዋቸው ጥንታዊ ባሕላዊ መንግሥታት መሪዎች በምርጫ ሥልጣን የሚይዙባቸው አከባቢዎች በርካቶች ነበሩ፡፡ ይህ አይነት የፖለቲካ ባሕል በሀገራችንም በአንዳንድ ብሔር ብሔረሰቦች ፖለቲካዊ ባሕል ውስጥ ይንጸባረቃል፡፡

ምርጫዎች በአጠቃላይ ሲታዩ በመንግሥት ጉዳይ የሕዝብን ተሳትፎ አማላካቾች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ብዙዎቹ ምርጫዎች የዜጎችን እኩልና ነፃ ተሳትፎ ሳያረጋግጡ የተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ብቻ ፍላጎታቸውንና ጥቅማቸውን የሚያራምዱበትና ብዙሃኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች የማይሳተፉባቸው ስለነበሩ የምልአተ-ሕዝቡን የሥልጣን ባለቤትነት ያረጋገጡ አልነበሩም፡፡ ከዜጎች ተሳትፎ አንጻር ሲታይ በባሪያ አሳዳሪዎች ሥርዓት ለምሳሌ እንደ አቴንስ ባሉ ጥንታዊት የግርክ ከተሞች ሕዝብ መሪዎቹን ይምርጥ ነበር ሲባል መራጭም ተመራጭም የነበሩት የባሪያ አሳዳሪዎች ብቻ ነበሩ፡፡ በበሪካታ የፊውዳላዊ የዘውድ አገዛዝ ሀገሮች ደግሞ በተለይም ለምርጫ ሊቀርቡ የሚችሉት መሳፍንቶች የመሬት ከበርቴዎችና ባላባቶች ነበሩ፡፡ በአንዳንድ ሀገሮችም የመምረጥ መብትን በፆታና በዘር ወይም በቀለም ላይ ተመሥርቶ በመገደብ ሴቶችና ጥቁሮች እንዳይጠቀሙበት ክልከላዎች ይደረጉ ነበር፡፡ የአብዩታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት (የሶሻሊዝም ሥርዓት) በሚከተሉ ሀገሮች ደግሞ በተለይም የመመረጥ መብት የአብዮተኞችና የአብዮቱ ደጋፊዎች መብት ብቻ ተደርጎ ነው የሚወሰደው፡፡ ዛሬ በበርካታ የዓለማችን ሀገሮች በዜጎች ነፃ ይሁንታ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎችን በማካሄድ ሕዝቡን የሥልጣን ባለቤት ማድረግ ቢቻልም ጥቅት በማይባሉ ሀገሮች የሚካሄዱት ምርጫዎች ግን የሕዝቦችን ነፃ ይሁንታ ለማረጋገጥ ሳይሆን በሥልጣን ላይ የመውጣታቸውና የመቆየታቸው ሕጋዊነት ከሕዝብ ፍላጎትና ይሁንታ የመነጨ ለማስመሰል ብቻ የሚካሄዱ ናቸው፡፡

አንድን ምርጫ ዴሞክራሲያዊና የሕዝብን ሉአላዊ ሥልጣን ያረጋገጠ እንዲሆን ለማድረግ ከተፈለገ ቢያንስ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሊሟሉ ይገባል፡፡

n (Universal Adult Frenchise) ሁሉም ከተወሰነ የዕድሜ ክልል በላይ የሆኑና የአዕምሮ ጤንነት ችግር የሌለባቸው ዜጎች በሌሎች ማናቸውም ምክንያቶች ልዩነት ሳይደረግባቸው በእኩልነትና በነፃነት ድምጽ የመስጠት መብታቸው በተግባር የሚከበርበትና የሚገለጽበት ሊሆን ይገባል፡፡

n (Multiparty System) ዜጎች እንደአመለካከታቸው በተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ድርጅቶች እንዲሁም በነፃ ማሕበራት በነፃነት የሚደረጁበት መብታቸውና የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶችና ፖሊሲዎችን ሚያራምዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ድርጅቶችም አማራጭ ሀሳቦቻቸውን በነፃነትና በእኩልነት መንፈስ ለሕዝብ የማቅረብና ሕዝቡን ከጎናቸው ለማሰለፍ ነፃ እንቅስቃሴ የሚያደርጉበት መብታቸው በሕግ ተረጋግጦና በትክክል ተከብሮ ሥራ ላይ መዋል አለበት፡፡

n (Free Press) የተለያዩ አማራጭ ሀሳቦችንና አመለካከቶችን ለሕዝቡ በሚዛናዊነት የሚያቀርቡና በነፃነት ሊሠሩ የሚችሉ የመገናኛ ብዙሃን ሊኖሩ ይገባል፡፡

n (Professional and Neutral Election Administration) በምርጫ የሚወዳደሩ አካላትን በባለሙያነትና በገለልተኝነት ለማስተዳደር የሚችል የሕዝቡን ነፃ ድምፅ የመስጠት መብት የሚያስከብር፣

ሕዝቡ የሰጠውን ድምፅ በትክክል እንዲቆጠርና እንዲገለጽ የሚያደርግና ከስርቆትና ከዘረፋ የሚከላከል ገለልተኛ የምርጫ አስተዳደር ሊኖር ይገባል፡፡

n (Neutral Local and International Observers) ገለልተኛ የሆኑ የሀገር ውስጥና አለም አቀፍ ታዛቢዎች በነፃነት ምርጫውን ታዝበው ምስክርነታቸውን የሚሰጡበት አሠራር መኖር አለበት፡፡

n (Periodical Election) ምርጫዎቹም በተወሰነ የጊዜ ገደብ የሚካሄዱ ሊሆን ይገባል፡፡

n (Independent Judiciary) በምርጫ ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን በነፃነት፣ በገለልተኝነትና በፍጥነት የሚዳኝ የዳኝነት ሥርዓት (አካል) ሊኖር ይገባል፡፡

እነዚህን ሁኔታዎች አሟልተው ምርጫዎችን የሚያካሄዱ ሀገሮች የመድበለ ፓርቲን ሥርዓት በአግባቡ የገነቡ ሲሆኑ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትም በአግባቡ የተገነባባቸውና ሕዝቡም በትክክል የሥልጣን ባለቤት የሆነባቸው ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲቋቋሙ የሚፈቅድ ሕገመንግሥትና ሕግ እያላቸውና በርካታ ፓርቲዎችም ተቋቅመው እያሉ ከዚህ በላይ የተገለጹትን የዴሞክራሲያዊ ምርጫ መስፈርቶች በትክክል በሥራ ላይ ባለማዋላቸው ሕዝቡ የሥልጣን ባለቤት ሊሆን ያልቻለባቸው ሀገሮችም ጥቂቶች አይደሉም፡፡ በአሁኑ ወቅት በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች እያሉባት ሕዝቧ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ሊያካሄድ ያልቻለባት ሀገራችን ኢትዮጵያም ከእነዚህ ሀገሮች ውስጥ አንዷ ሆናለች፡፡ ስለዚህም በሀገራችን የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃ፣ ፍትሐዊ፣ ዴሞክራሲያዊና የሕዝባችንን የሥልጣን ባለቤትነት በትክክል ሊያረጋግጡ የሚችሉ እንዲሆኑ ለማድረግ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች በትክክል ሥራ ላይ ማዋል ይጠበቅብናል፡፡

1-ምርጫዎችና ችግሮቹ በኢትዮጵያ፡-

በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ-መንግሥት ሀገራችን የዓለም መንግሥታት ማሕበር አባል ለመሆን ላቀረበችው ጥያቄ እንዲታሟላ ከተጠየቀችው ጥያቄዎች አንዱ በሕዝብ የተመረጠ ፓርላማ (ሕግ አውጪ አካል) ሊኖራት ይገባል የሚል ስለነበረ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ የተሰጠ ለማስመሰል በሀገራችን የፓርላማ አባላት ምርጫ ማካሄድ ተጀምሯል፡፡ ይሁን እንጂ በዘውዳዊው ሥርዓት ዘመን ሲካሄዱ የነበሩት የፓርላማ አባላት ምርጫዎች ለገዥው የፊውዳል መደብ ተጨማሪ ሕጋዊ የመግዛት መብት ያጎናጸፉና በተለይም ለዘውዳዊው አገዛዝ ፍጽማዊ የፈላጭ ቆራጭነት መብቱ እንዳይነካ የተቀረጹና ሥራም ላይ ስውሉ የነበሩ ናቸው፡፡ በስርዓቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲቋቋሙም ሆነ በምርጫ እንዲወዳደሩ የማይፈቀድ ስለነበረ አማራጭ ፖሊሲዎችም ሆኑ የፖለቲካ አመለካከቶች ለሕዝብ የሚቀርቡበትና ሕዝቡ የሚወስንበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ በግለሰብ ደረጃም ቢሆን የሀብት ማለትም የመሬትና የከፍተኛ ቋሚ ንብረት ባለቤት ያልሆኑ ዜጎች ለውድድር የማይቀርቡበት ስለነበረ የፊውዳል ሥርዓት ገዥ መደብ አባላት ማለትም ሰፊ መሬትና ከፍተኛ ቋሚ ንብረት ያለቸው ሰዎች ከበሬታና ጥቅም ለማግኘት የሚሽቀዳደሙበት ድራማ ብቻ ነው የነበረው፡፡ ይሁን እንጂ ይህም ድራማ በሥርዓቱ ገዥዎች በተለይም በንጉሠነገሥቱ #ትክክለኛና ዴሞክራሲያዊ$ እየተባለ ይነገር ነበረ፡፡

በደርግ ሥርዓት ደግሞ አገዛዙ ሥልጣን ላይ የወጣው በጠመንጃ አፈሙዝ ስለነበረ ይህንኑ አገዛዛቸውን የሕዝብ ይሁንታ ያለው ለማስመሰል የሕግ አውጪ አካሉን (የብሔራዊ ሼንጎውን) አባላት ምርጫ በየአራት አመቱ ሲካሄድ ነበር፡፡ ቢሆንም ግን ሥርዓቱ አንድ ብቸኛ መሪ ፓርቲ (ኢሠፓ) እንጂ ሌሎች ፓርቲዎች በሀገሪቱ እንዲኖሩ የማይፈቅድ ስለነበረ የዚሁ መሪ ፓርቲ ፖሊሲ አራማጆችና አባላትን እንጂ ሌሎች ፓርቲዎችና ዜጎች አማራጭ ሀሳብ ይዘው ለውድድር የሚቀርቡበት አልነበረም፡፡ በዚህም ምክንያት ሌላ አማራጭ በሌለበት ብቸኛው ገዥ ፓርቲ የሚያቀርባቸው ዕጩዎች ሕዝቡ ወደዳቸውም አልወደዳቸውም ሕዝቡን ወክለዋል ተብለው በገዥው ፓርቲ የሚሰየሙበት ሂደት ነው የነበረው፡፡ ስለዚህም ሥርዓቱ ምርጫ እያለ በሚያዘጋጃቸው ግርግሮች የሕዝብ ገንዘብና ንብረት ከመባከኑ በስተቀር ነፃ ምርጫና የህዝብ ውክልና የሚባል ነገር በተግባር አልነበረም፡፡

በኢህአዴግ አገዛዝ በተለይም በሽግግር ወቅት ቻርተርናበኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት ዜጎች የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ማቋቋም እንደሚችሉ ስለተደነገገ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሕዝቡም ይህንኑ መብታቸውን ለመጠቀም

ጥረቶችን አድርገዋል፡፡ እያደረጉም ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የኢህአዴግ ሥርዓት የሚከተለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የፖለቲካ ፍልስፍና በሕግ የበላይነት የማይመራና ራሱ ላወጣቸው ሕጎችና ሕገመንግሥትም የማይገዛ በመሆኑ በቻርተሩና በሕገመንግሥቱ የተደነገጉት መብቶች በሥራ ላይ ሊውሉ አልቻሉም፡፡ ድንጋጌዎቹ በኢህአዴግ አገዛዝ የወጡበት ምክንያትም ኢህአዴግ የሕዝቡን የሥልጣን ባለቤትነት በተግባር ለማረጋገጥ ስለፈለገ ሳይሆን ስልጣን በያዘበት ወቅት በሶሻሊዝምና በካፒታሊዝም መካከል ሲካሄድ የነበረው ቀዝቃዛው ጦርነት አብቅቶ የዓለማችን ፖለቲካ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓትን የግድ ባለበት ወቅት ስለነበረ የዘመኑን ፋሽን ለመልበስና ዴሞክራሲያዊ ለመምሰል ብቻ እንደነበረ በአተገባበር ሂደቱ በሚፈጥራቸው በርካታ መስናክሎች ግልጽ ሊሆን ችሎአል፡፡ በዚህም ምክንያት ባለፉት አራት አገር አቀፍ ምርጫዎችና በርካታ የአከባቢ ምርጫዎች ወቅቶች በሰላማዊ መንገድ ዓላማቸውን ለማራመድ በሕግ መሠረት ተመዝግበውና ሰርቲፍኬት አግኝተው ያሉ ፓርቲዎች በነፃነት ዓላማቸውን እንዳያራምዱና እንዳይንቀሳቀሱ እንዲሁም ጠንካራ ተወዳዳሪዎች ሆነው እንዳይገኙ፡-

—በርካታ አባሎቻቸውን በሰበብ አስባቡ  ከመንግሥት ሥራ እንዲወጡ፣ እንዲታሰሩ፣ በረሀብና በችግር እንዲንገላቱና ከሀገር እንዲሰደዱ በማድረግ፣

—በመንግሥት በጀትና ዓለም አቀፍ ዕርዳታ የሚሠሩ የትምህርት ተቋማት የሚሰጡዋቸው ነፃ የትምህርት ዕድሎች ለአባላቶቹና ለደጋፊዎቹ ብቻ እንዲሆን በማድረግና ሌሎች ዜጎች በሙያ ብቃታቸው ተወዳድረው የሚያገኙበትን ዕድል በመዝጋት፣

—ከየትምህርት ተቋማት የሚመረቁ ወጣቶችም በስራ ላይ ለመሠማራት ከፈለጉ   የግዴታ የኢህአዴግ አባላት እንዲሆኑ ካልሆኑ ግን ለሥራ አጥነት እንዲዳረጉ በማድረግ፣

— በገጠርም ወጣት አርሶ አደሮች የእርሻ መሬት ለማግኘትም ሆነ የተለያዩ መንግሥታዊ አገልገሎቶችንና ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት የኢህአዴግ አባላት እንዲሆኑና ከተቃዋሚ ፓርቲ አባልነት እንዲርቁ የሚያስገድዱ ተጽኖዎችን በማድረግ፣

— ለራሱ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን፣ ከመንግሥት ደመወዝ የሚከፈላቸው ሠራተኞችንና የተለያዩ ንብረቶችን ለጽ/ቤቶቹ በማንአለብኝነት እየተጠቀመ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ግን ለጽ/ቤትም ሆነ ለመሰብሰቢያ አዳራሽ በክራይ እንኳ ለማግኘት እንዳይችሉ የተለያዩ ቢሮክራሲያዊ ተጽኖዎችና አከራዮችን የማስፈራራት ተግባራትን በመፈጸም፣

— በምርጫ ሂደት ወቅቶችም ምርጫዎችን የሚያስፈጽሙት ሠራተኞች ተወዳዳሪ ፓርቲዎች በተሳተፉበት ገለልተኝነታቸው እየተረጋገጠ እንዳይመለመሉና በራሱ በገዥው ፓርቲ ካድሬዎች ብቻ ተመልምለው ለኢህአዴግ አሸናፊነት እንዲሠሩ በማድረግ፣

— ገለልተኛ የሀገር ውስጥና አለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢዎች ምርጫዎችን በነፃ የሚታዘቡበት ሁኔታ እንዳይኖር በማድረግና የሕዝብ የምርጫ ታዛቢዎችም ግልጽነት በጎደለው አሰራር እየተመለመሉ እንዲቀመጡ በማድረግ፣

— በተለይም ከ 2002 ምርጫ ጀምሮ ሕዝቡን በ 1 ለ 5 የምርጫ ሠራዊት ጠርንፎ ድምጹን በጠርናፊዎች ቁጥጥር እንዲሰጥ በማድረግ፣

— ነፃ የሙያና የሲቪክ ማህበራት ኖረው ምርጫን በነፃነት እንዳይታዘቡና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋፆ እንዲያበረክቱ አፋኝ ሕጎችን በማውጣትና የራሱ ተቀጽላዎች የሆኑ ማሕበራት ብቻ የታዛቢነት ሥራ እንዲሠሩ በማድረግ፣

— ከመንግሥት ለፖለቲካ ፓርቲዎች ድጋፍ የሚሰጠውን ገንዘብ የመደበኛ ሥራ ድጎማውን ጠቅልሎ ከወሰደ በኋላ ከሕግ ውጪ ራሱ ለፈለጋቸው  ፓርቲዎች እውነትን አዛብተው እንዲመሰክሩለት በመደለያነት እየሰጠ፣ ለምርጫ ቅስቀሳ ሥራ የተመደበውን ደግሞ ለዚሁ ጉዳይ በተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ላይ ከተቀመጠው መመዘኛ ውጭ #በተወካዮች ምክር ቤ/ት ባላቸው$ መቀመጫ በምል ሰበብ የምርጫ ቦርድ ባበረከተለት ሕገ-ወጥ ሊገሳ በተጨማሪ በመውሰድና

— የምርጫው ሂደት በአግባቡ እንዳይዘገብ በነፃ ሚዲያዎች ላይ የሚያከሄደውን ወከባና አፈና አጠናክሮ ከሥራ

ውጭ በማድረግ በሥርዓቱ ዘመን የተካሄዱት ምርጫዎች ዴሞክራሲያዊና ሕዝቡን ለሥልጣን የሚያበቁ እንዳይሆኑ አድርጎአቸው ይገኛል፡፡

ስለዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለፉትና አሁን በስልጣን ላይ ባለው መንግሥት ዘመናት ነፃ፣ ፍትሐዊና ታአማንነት ያለው ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እየተመኘና እየታገለለት ቢሆንም በተግባር ሊያየውም ሆነ በእነዚህ መንግሥታት በተካሄዱት ምርጫዎች አማካይነት የሥልጣን ባለቤት ሊሆን አልቻለም፡፡

2- የአምስተኛ ዙር ሀገር አቀፍ ምርጫ ዝግጅትን በሚመለከት፡-

—በአምስተኛው ዙር የምርጫ ዝግጅት ወቅት ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የሀገራችን የምርጫ ጉድለቶች ተወግደው ሕዝባችንን በትክክል የሥልጣኑ ባለቤት ሊያደርግ በሚችል ሁኔታ እንዲካሄድ ለማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ በቀና መንፈስ ውይይትና ድርድር ለማካሄድ መድረክ በተደጋጋሚ ለገዥው ፓርቲ ጥሪዎችን ሲያደርግ ቢቆይም በትጥቅ ትግል ሥልጣን ለመያዝ እየተንቀሳቀሱ ካሉት ፓርቲዎች ጋር እስከ ውጭ ሀገር ድረስ እየተመላለሰ የሚደራደው ኢህአዴግ ለመድረክ ሰላማዊና ሕጋዊ ጥሪ እስከአሁን ድረስ በፍጽም አዎንታዊ ምላሽ አልሰጥም ብሎ በአሻፈረኝ ባይነት ቀጥሎበታል፡፡

—በኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ በኩልም ከዚህ በላይ በአጭሩ የተጠቀሱት ችግሮች እንዲወገዱና ለነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ በማድረግ የበኩሉን አዎንታዊ ሚና እንዲጫወት መድረክና ሌሎች በሰላማዊ አግባቢ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች በተለያዩ ወቅቶች ላቀረብናቸው ጥያቄዎች ቦርዱ እስከአሁን ተጨባጭ የሆነ አዎንታዊ ምላሽ አልሰጠም፡፡

—የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በየምርጫው ሂደቶች በጉልህ የታዩትን ምርጫው በዴሞክራሲያዊ አግባብ እንዳይካሄድ እንቅፋት የነበሩ ሁኔታዎችን በተጨባጭ እያቀረብን ተገቢው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ለጠየቅናቸው ጥያቄዎች ምላሽ ለማስገኘት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ከመወያየት ይልቅ ፓርቲዎችን ጠርቶ የምርጫ ሰሌዳና በጀት ለማጸደቅና ለማወጅ በመጣደፉ ባለፉት የምርጫ ሂደቶች የነበሩ ችግሮቻችን አሁንም እንዳሉ ናቸው፡፡

—ምርጫውን እንዲያስፈጽሙ በየአከበቢው ተመድበው የሚገኙ አባላትም ባለፉት አራት ምርጫዎች ወቅት በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ በርካታ በደሎችን በመፈጸማቸው ቅሬታ ስናቀርብባቸው የቆየን ሰዎች ናቸው፡፡

—የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫን በሚመለከትም ተቃዋሚዎችም ሆኑ ሕብረተሰቡ በአግባቡ በየአከባቢው ቦታና ሰዓቱ በግልጽ በተነገረ የስብሰባ ጥሪ ተጠርተው መሳተፍ ሲገባቸው ውስጥ ለውስጥ በድርጅታዊ መስመር በተደረገ ጥሪ ተመርጠው ተዘጋጅተዋል፡፡

—ከመንግሥት ለፖለቲካ ፓርቲዎች ለመደበኛ ሥራቸው የሚመደበውን በጀት ገዥው ፓርቲ በሕግ ከተቀመጠው አላማ ውጭ ለወዳጅ መግዣ ሲጠቀምበት ምርጫ ቦርድ ሕጋዊነት ለሌለው አሰራር እውቅና መስጠት ብቻ ሳይሆን በቀጥታ እጁን አስገብቶበት ሲያከፋፍል ቆይቷል፡፡

—ለምርጫ ተግባር ከመንግስት የተመደበውን በጀትም በተሻሻው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁ/573/2000 አንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 45 ንዑስ ቁጥር 2 ሀ እና ለ ላይ በግልጽ ከተቀመጠው መስፈርት ውጭ ለገዥው ፓርቲ በመመደብ ተገቢ ያልሆነ ወገንተኝነት እያሳየ ይገኛል፡፡

—መድረክ ምርጫ ከመካሄዱ በፊት የምርጫው ሜዳ እንዲስተካከል ለመጠየቅ በአዲስ አበባ ከተማ የጠራውን ሰላማዊ ሰልፍ የከተማው አስተዳደር እውቅና ሰጥቶ እያለ ኢህአዴግ በሌላ እጁ ሰልፍ እንዲታደረጉ እንጂ ለሰልፉ ቅስቀሳ እንዲታደርጉ አልተፈቀደላችሁም በምል በተለመደና ግራ በሚያጋባ ተጽኖ በምርጫው ሂደት ያሉትን ችግሮች ለሕዝቡ በሰፊው እንዳናሳውቅ ከፍተኛ ጫና ሲያደረግብን ቆይቷል፡፡

—በአንዳንድ አከባቢዎች ለምርጫ ሥራ መንቀሳቀስ የጀመሩ አባሎቻችንን በሰበብ አስባቡ ማሰርና መዋከብም ተጀምሯል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ባሉበት ሁኔታ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድና የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ የሚያስችል እንደዚሁም ለፖለቲካ ፓርቲዎች ነፃ የምርጫ ውድድር የተመቻቸ ሁኔታ ተፈጥሯል

ብለን ለማመን እንቸገራለን፡፡

3-የምርጫ ስነ-ምግባር ደንቡ ለምርጫው ስኬት ያለው እደምታ፣

— የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ለሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሂደት እውን መሆን አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ፣ የተሟላና ሁሉም ተወዳዳሪዎች በትክክል የሚያከብሩት የምርጫ ስነ-ምግባር መኖር እንዳለበት በጥብቅ ያምናል፡፡ ስለዚህም ይህንን ደረጃውን የጠበቀና የሀገራችንን ተጨባጭ ችግሮች ሊፈታ የሚያስችለን ስነ-ምግባር ከገዥው ፓርቲ ጋር ተደራድረን ለማውጣት ስንጠይቅ ቆይተናል፡፡ ገዥው ፓርቲ ግን በአሻፈረኝ ባይነት ቀጥሎበታል፡፡

— ኢህአዴግ ደረጃውን የጠበቀ የተሟላ የምርጫ ስነ-ምግባር በሀገራችን እንዲኖር ከመሥራትና ከመተባበር ፋንታ ከስነ-ምግባር ክፍሎቹ ውስጥ አንዱን ማለትም በምርጫ ውድድር ወቅት ፓርቲዎች ሊኖራቸው ስለምገባው ግንኙነት የሚገልጸውን ክፍል ብቻ ወስዶ የሀገራችንን መሠረታዊ የምርጫ ችግሮች የሚመለከቱ ሁለት ክፍሎችን ቆርጦ አስቀርቷል፡፡ እነዚህም ተቆርጠው የቀሩት ክፍሎች ሙያዊና ገለልተኛ የምርጫ አስተዳደር (Ethical and Professional Administration of Elections) እና አለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢነት መርህ (Declaration of principles for International Election observation and code of Conduct for International Observers) የሚባሉ ክፍሎች ናቸው፡፡

— በመድረክ እምነት ኢህአዴግ ይህንን ያልተሟላ የምርጫ ስነ-ምግባር ብቻ ይዘን እንዲንጓዝ የሚፈልግበት ዋና ምክንያትም በምርጫዎቹ ሂደቶች የሚፈጽማቸውን ሕገ-ወጥና ኢ-ዴሞክራሲያዊ ተግባራት በብቃት የሚቆጣጠር ገለልተኛ የምርጫ አስተዳደርና ገለልተኛ የምርጫ ታዛቢ እንዳይኖሩ ስለሚፈልግ ብቻ ነው፡፡

— ኢህአዴግ የምርጫ ስነ-ምግባርን በሚመለከት ያመጣው ችግር የተሟላ እንዳይሆን ማድረግ ብቻ ሳይሆን የፈረመውንና ሕግ አድረጎ ያወጣውን ስነ-ምግባር ተከትሎ የተወዳዳሪ ፓርቲዎችን መብቶች አክብሮ አለመንቀሳቀሱና በተደጋጋሚ መጣሱም ጭምር ነው፡፡ ስለዚህም የስ-ምግባር ፍረማው ኢህአዴግ ከሕግ ውጭ ከሚለግሳት ገንዘብ በስተቀር ከፓርቲዎች መብት አጠባበቅ አንጻር ተጨባጭ ውጤት እንዳላመጣ የተረዱ መጀመሪያ ፈርመው ከነበሩ ፓርቲዎች አንዳንዶቹ ፈራሚዎች ካቋቋሙት ም/ቤት ጥለው ሲወጡ ለማየት ችለናል፡፤

ስለዚህም የምርጫ ስነ-ምግባሩ የተሟላ ባለመሆኑና ለፕሮፓጋንዳ ያህል ቢፈረምም እንደሌሎች የሀገራችን ሕጎች ሁሉ ተገቢውን ክብር ከገዥው ፓርቲ ያላገኘ በመሆኑ ለምርጫው ዴሞክራሲያዊነትና ስኬት ተገቢውን ሚና ሊጫወት አልቻለም፡፡

3-  ከኢህአዴግና ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር አብሮ የመስራት ዝግጁነት በሚመለከት፡-

—መድረክ ከኢህአዴግና ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ያለው የፖለቲካ አመለካከትና አስተሳሰብ ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩነታችን ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፃና ፍትሐዊ ምርጫ አማካይነት ለሚሰጠው ውሳኔ ሁላችንም ተገዥዎች ሆነን የጋራ ሀገራችንን በጋራ እንዲንገነባ አጥብቆ ይፈልጋል፡፡ #የእኔ አመለካከት ብቻ ሥራ ላይ ይዋል፣ ከልሆነ ሁሉም ነገር ይቅር$ የሚል ጠባብ የቡድን አስተሳሰብ የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም የሚጎዳ ስለሆነ ዴሞክራሲያዊም ሆነ ሕዝባዊ አስተሳሰብ አይደለም ብሎ ያምናል፡፡ ስለዚህም ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ያለንን ልዩነት ለሕዝብ ውሳኔ ትተን በምንስማማባቸው ጉዳዮች ላይ በጋራ ቅንጅትና ግንባር ፈጥረን እንዲንታገልና ከኢህአዴግ ጋር ያለንን ልዩነትም በቀና ውይይትና ድርድር ለመፍታት ጥረቶችን ስናደርግ ቆይተናል፡፡ ለወደፊቱም በዚሁ እንቀጥልበታለን፡፡

— በ 2007 የምርጫ ዝግጅትና ሂደት ወስጥም ምርጫው ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ሕዝባችንን ለሥልጣን ባለቤትን የሚያበቃ ሆኖ እንዲካሄድና እንዲጠናቀቅ የበኩሉን ድርሻ ለማበርከት መድረክ ዝግጁ ነው፡፡

4- ለምርጫው ስኬት ከባለ ድርሻ አካለት የሚጠበቅ ኃላፊነት፡-

ምርጫው የሚመለከታቸው ዋነኛ ባለድርሻ አካላት መንግሥትና ገዥው ፓርቲ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ ምርጫ ቦርድና

ምልአተ-ሕዝቡ ናቸው፡፡ ስለዚህም ከእነዚህ ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአጭሩ እንደሚከተለው ለማቅረብ እሞክራለሁ፡፡

5-1- ከመንግሥትና ገዥው ፓርቲ የሚጠበቁ ተግባራት፡-

n ከተቃዋሚ ፓርቲዎች እስከአሁን እየቀረበለት ላለው የድርድር ጥያቄ እየሰጠ ያለውን የአሻፈረኝ ምላሽ አቁሞ በሀገራችን በአሁኑ ወቅት ባለው የፖለቲካ ምህዳር ችግሮች ዙሪያ ከሰላማዊና ሕጋዊ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በቀና መንፈስ ውይይት ማካሄድና ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ነፃ እንቅስቃሴና በምርጫ ለመወዳደር ተስማሚ ወይም ሳቢ የሆነ ሁኔታ (Conducive Environment) መፍጠር፣

n ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመወያየት የፖለቲካ ፓርቲዎችንም ሆነ ምርጫን በሚመለከቱ ሕግ ነክ ጉዳዮች የስነ-ምግባር ኮዱንም ጨምሮ ዴሞክራሲያዊ ምርጫን በሀገራችን በተሟላ መልኩ ሥራ ላይ ለማዋል በሚያስችል ደረጃ እንዲስተካከሉ ማድረግ፣

n የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን እንደ ፓርቲ ንብረት ለራሱ ያለገደብ እየተጠቀመ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ሀሳቦች በአግባቡ እንዳያስተናግዱ የሚፈጽምባቸውን ጫና አቁሞ በሕገመንግሥቱ በተጣለባቸው ኃላፊነት መሠረት የተለያዩ መረጃዎችና የተቃዋሚ ፓርቲ አስተያየቶችንም በሚዛናዊነት ለሕዝቡ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣

n ለሕግ የበላይነት መገዛትና ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ከሚደርሰው የመንግሥት ድጋፊ ውጭ የሆነውን የመንግሥትን ሀብትና ንብረት መንግሥታዊ ሥልጣንን መከታ አድረጎ ለራሱ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ከማዋል መቆጠብ፣ ከመንግሥት በሕጉ መሠረት የሚሰጠውን ድጋፊም በሕጉ ለተጠቀሰው ዓላማ ብቻ መጠቀምና ሌሎች ፓርቲዎችን ለመደለል ማዋሉን ማቆምና ሁሉም በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ፍትሐዊ በሆነ አግባብ ከመንግሥት ድጋፍ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲመቻች ተባብሮ የድርሻውን መወጣት፣

n ሕብረተሰቡ በነፃነት የመምረጥ መብቱን እንዳይጠቀም ለመቆጣጠርና ጫና ለማሳደር ከ 2002 ዓ ም ጀምሮ ያቋቋመውን የ 1 ለ 5 የምርጫ ሠራዊት ማፍረስና ፀረ-ዴሞክራሲያዊና ሕገወጥ እንቅስቃሴውን እንዲያቆም በማድረግ የሕዝቡን ነፃ የድምፅ አሰጣጥ መብት ማክበርና ማስከበር፣

n የምርጫ አስተዳደሩን ገለልተኛነት ለማዛባት በምርጫ አስፈጻሚዎችና የሕዝብ ታዛቢዎች አባላቱንና ደጋፊዎቹን ማስገባቱን ማቆም፣

n ገለልተኛ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ታዛቢዎች ምርጫዎችን እንዲታዘቡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

n በምርጫዎች ወቅት በከፍተኛ ደረጃ የታጠቁ ኃይሎችን በሕዝቡ ውስጥ በማሰማራት ሕዝቡን ማስፈራራቱን ማቆምና የጸጥታ አስከባሪዎች ገለልተኛነታቸውን ጠብቀው እንዲሠሩ ማድረግ፣

n በምርጫ ሂደት በሚከሰቱ ችግሮች ላይ ከሁሉም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ጋር በእኩልነትና ቀና መንፈስ በመወያየት ችግሮቹን ለመፍታት መንቀሳቀስ፣

5-2- ከምርጫ ቦርድ የሚጠበቅቁ ተግባራት፡-

n በየደረጃው ያሉት አካላቱ በትክክል ከገዥው ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ነፃና ገለልተኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ እስከአሁን በተካሄዱ ምርጫዎች በተቃዋሚ ፓርቲዎችና በአባላቶቻቸው እንቅስቃሴ ላይ ግልጽ የሆነ አድሎአዊ ተግባር በፈጸሙና የምርጫ እንቅስቃሴዎቻቸውን ሲያደናቅፉ በነበሩት የምርጫ አስፈጻሚዎች ላይ ተጨባጭ የሆነ የዲስፐሊን እርምጃዎችን መውሰድና ከቦታው ማንሳት፣

n የተቃዋሚ ፓርቲዎች እስከአሁን በተካሄዱት የምርጫ እንቅስቃሴዎች የታዩትን ጉድለቶች ለማረም እንዲቻል ያቀረቡትን የውይይትና የድርድር ጥያቄዎችን በቸልታና በመሸፋፈን ማለፉን ትቶ ተጨባጭ መፍትሔዎችን ለማስገኘት የበኩሉን ኃላፊነት መወጣት፣

n በ 2007 የምርጫ እንቅስቃሴ ወቅቶች ለሚከሰቱ ችግሮች ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የባለድርሻዎች የጋራ

መድረክን በብቃትና በገለልተኝነት በመምራት ለሚከሰቱ ችግሮች ፈጠን መፍትሔዎችን የመስጠት ኃለፊነቱን መወጣት፣

n ገለልተኛነቱን ጥያቄ ውስጥ በሚከት ሁኔታ ከመንግሥት ለፖለቲካ ፓርቲዎች መደበኛ ሥራ የሚመደበው በጀት ከሕግ ውጭ የስነ-ምግባር ፊርማን በማሳበብ ለአንዳንድ ፓርቲዎች በማከፋፈሉ ሂደት እጁን ማስገባቱን ለወደፊቱም እንዲያቆምና ገንዘቡን ለሁሉም በሰላማዊ አግባብ ለሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች በፍትሐዊነት ለማከፋፈል የሚያስችል ሕግ እንዲወጣ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ፣

n በምርጫ ለሚወዳደሩ ፓርቲዎች በተለይ የሚመደበው በጀትም በሕጉ ላይ በተቀመጡት ሁለት መመዘኛዎች ማለትም ፓርቲዎች በሚያቀርቡት እጩዎች ብዛትና በሴት ዕጩዎች ብዛት ብቻ እንዲከፋፈል ማድረግና ለምርጫ ተግባር የሚውለውን በጀት በሚመለከት በሕጉ ያልተጠቀሰውን የፓርላማ መቀመጫ መመዘኛ ተጠቅሞ ለገዥው ፓርቲ ከመስጠት መቆጠብ፣

n ገለልተኛ የሀገር ውስጥና አለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢዎች ምርጫውን እንዲታዘቡ በአግባቡና በወቅቱ መጋበዝ፣ የሕዝብ የምርጫ ታዛቢዎችን የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ሕዝቡ በአግባቡ ተጠርቶ በተሳተፈበት ግልጽ ምርጫ እንዲመረጡና ገለልተኛነታቸውም እንዲረጋገጥ ማድረግ፣

5-3- ከተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚጠበቁ ተግባራት፡-

n እስከአሁን በታዩት የፖለቲካ ምህዳርና የምርጫ ሂደት ችግሮች ላይ ከገዥው ፓርቲና ከመንግሥት እንዲሁም ከምርጫ ቦርድ ጋር በሰላማዊ ውይይት መፍትሔ ለማስገኘት የሚያደርጉትን ጥረቶች አጠናክሮ መቀጠል፡፡

n በሰላማዊ ትግሉ ላይ ተስፋ አለመቁረጥና ሕዝቡም ተስፋ እንዳይቆርጥ ማበረታታት፣

n የጋራቸው የሆኑ ችግሮችን በተላይም ገዥው ፓርቲ በሁሉም ላይ የሚፈጽማቸውን ተጽኖዎች ለመቋቋም ተባብሮ የጋራ ጥረቶችን ማድረግ፣

n በፖሊሲና በአመለካከት መርሆዎች ላይ ተመሥረቶ መቀራረብና በተቻለ መጠን ሕዝቡ ለጠየቃቸው የግንባርና የውህደት ጥያቄዎች አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት ጥረት ማድረግ፣ ቀደም ስል የመሰረቱዋቸውን ጥምረቶች (ቅንጅቶችና ግንባሮችን) በሰበብ አስባቡ ከማፍረስ መቆጠብና የደረሱባቸውን ስምምነቶችም አክብሮ በመስራት ሕዝቡ የበለጠ ተስፋ የሚጥልባቸው ሆኖ መገኘትና በዚህ ረገድ ከዚህ በፊት የፈጸሙዋቸውን ስህተቶችን በፍጥነት ማረም ይጠበቅባቸዋል፡፡

5-4- ከምልአተ-ሕዝቡ የሚጠበቁ ተግባራት፡-

n የኢትየጵያ ሕዝብ የሀገራችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ዋነኛው ባለቤት ስለሆነ በሂደቱ እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮችን በንቃት መከታተልና በሀገራችን የሚካሄዱ ምርጫዎች የሥልጣን ባለቤትነቱን በሚያረጋግጥና አምባገነንነትን ከሀገራችን ሊያስወግድ በሚያስችል መልኩ ተግባራዊ እንዲሆ በጽናት መታገል ይጠበቅበታል፡፡

n ሕዝብ በፖለቲካ ጉዳዮች ቸልተኝነትና ስንፍና በሚያሳይበት ሀገር አምባገነንነት መስፈኑ ስለማይቀርና አምባገነንነት ደግሞ ለቀጣዩ የሀገራችንና የሕዝባችን ሕልውና አደጋ ደቃኝ ስለሆነ በተለይም የተማረውና በሀገራችን የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደቶች እየታዩ ያሉትን ችግሮች በሚገባ ሊረዳ የሚችለው ምሁሩ የሕብረተሰባችን ክፍል በግል ኑሮ ላይ ብቻ ማተኮሩን ትቶ እነዚህ አሁን በሀገራችን እየታዩ ያሉት የዴሞክራሲ ግንባታ ችግሮች ወደፊት በሀገራችንና በሕዝባችን ሕልውና ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን አደጋዎች በማስቀረት በኩል ኃላፊነቱን በተጨባጭ ሊወጣ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ሁላችንም ባለድርሻ አካላት የሀገራችን የዴሞክረሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደትና ሰላማዊ ትግላችን በአሁኑ ወቅት አሳሳቢ በሆነ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ተገንዝበን ይህንን የሀገራችንን ሕልውና ሊፈታተን የሚችለውን ችግር ከሁላችንም ቁጥጥር ውጭ ከመሆኑ በፊት ለ 2007 ምርጫ በምናደርገው ዝግጅት በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት በመንቀሳቀስ ችግሮቹን በሰላማዊ ውይይትና ድርድር ለመፍታት የየበኩላችንን ድርሻ መወጣት ይጠበቅብናል፡፡ ለችግሮቻችን የሰላማዊ መፍትሔ ተስፋን ለማለምለም ድርሻችንን ለመወጣት ብቁዎች ነን ወይስ አይደለንም ለምለው ጥያቄ በተጨባጭ ምላሽ መስጠት የምገባን ወቅት አሁን እንደሆነም ማጤን ይኖርብናል፡፡ ከዚህ በፊት የነበሩ ደካማ

ጎኖቻችንን አይተን ለምርጫው ሰላማዊነት፣ ዴሞክራሲያዊነትና ስኬታማነት የምንጫወተው ሚና በሀገራችን ታሪክ ትልቅ ሥፍራ እንደምኖረው እረዳለሁና ሁላችንም ይህንን ተገንዝበን በርትተን እንሥራ እላለሁ፡፡